

# የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የትምህርት ቤት የክትባት ፖሊሲ

## በተደጋጋሚ የተጠየቁ ጥያቄዎች - የትምህርት ቤት ክትባት መስፈርቶች (ለቤተሰቦች)

የዲስትሪክት ህግ[1] እና ደንቦች[2] በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ያሉ ትምህርት ቤቶች እንደ ምዝገባ እና በትምህርት ቤት የመገኘት ቅድመ ሁኔታ ተማሪው የህጻናት የክትባት መስፈርቶችን[3] ያሟሉ መሆኑን እንዲያረጋግጡ ያስገድዳል። ተማሪው ግዴታውን ካላሟላ፣ትምህርት ቤቱ የጎደለውን ክትባት(ቶች)ን በሚመለከት ወዲያውኑ በጽሁፍ ለወላጅ፣ሞግዚት፣ወይም አካለመጠን ለደረሰ ተማሪ እንዲያሳውቅ ይገደዳል።

**በpre-K 3፣ መዋለህጻናት፣ 7ኛ ወይም 11ኛ ክፍል ያለ/ች ተማሪ ከዲሴምበር 9፣ 2024 በፊት ትእዛዙን ካላከበረ/ች፣ የክትባት ማረጋገጫው ለትምህርት ቤቱ እስኪደርስ ድረስ ትምህርት ቤቱ ተማሪውን/ዋን በጊዜያዊነት ከትምህርት ቤት እንዲያገልል ይገደዳል።**

### 1። ክትባቶች (ክትባቶች) አስፈላጊ የሚሆኑት ለምንድን ነው?

ክትባቶች እንደ ኩፍኝ ያሉ በጣም ተላላፊ እና ለህጻናት አደገኛ ሊሆኑ የሚችሉ በሽታዎችን ስርጭት ለማቆም ስለሚያግዙ በጣም አስፈላጊ ናቸው። የሁሉም ሰው ደህንነት ለመጠበቅ፣ ሁሉም ተማሪዎች ክትባታቸውን ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ሊከተቡ ይገባል። የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከላት (CDC) ስለ ክትባቶች የተለመዱ ጥያቄዎች፣[4] የክትባት ውሳኔ መወሰን፦ ለተለመዱ ስጋቶች ምላሽ መስጠት፣[5] እና የሁማን ፓፒሎማቫይረስ ክትባት (ክትባት) የሚለውን ጨምሮ ክትባቶች ለምን እንደሚያስፈልጉ የሚገልጽ መረጃ አለው።[6]

### 2። ለልጄ የሚያስፈልጉት የትኞቹ ክትባቶች ናቸው?

DC Health ልጅዎ በእድሜያቸው መሰረት የትኞቹ ክትባቶች እንደሚያስፈልጋቸው ወስኗል።[7]የሚያስፈልጉትን ክትባቶች ዝርዝር ለማግኘት የ DC Healthን የክትባት መስፈርቶች[3] ይመልከቱ።

### 3። ልጄ የትኞቹን ክትባቶች አስቀድሞ የወሰደ መሆኑን እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

ልጅዎ የትኞቹን ክትባቶች እንደወሰደ ማወቅ ከፈለጉ፣ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ የልጅዎን የክትባት መዛግብት ቅጂ እንዲሰጥዎ መጠየቅ ይችላሉ። እንዲሁም ለ DC Health የክትባት ፕሮግራም በ(202) 576-7130 መደወል ይችላሉ።

### 4። ልጄ መከተቡን የልጄ ትምህርት ቤት እንዴት ያውቃል?

ልጅዎ በኮሎምቢያ ዲስትሪክ ውስጥ በሚከተብበት ጊዜ፣ የጤና እንክብካቤ አቅራቢው ወደ ኮሎምቢያ ዲስትሪክት የክትባት መረጃ (DOCIIS) ስርዓት ያክለዋል። ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች አስፈላጊ የሆኑ ክትባቶች መከተባቸውን ለማጣራት DOCIISን ይጠቀማሉ። እንዲሁም ትምህርት ቤቶች የልጅዎን ክትባቶች የወረቀት መዛግብት በጤና ፋይሎቻቸው ውስጥ ሊይዙ ይችላሉ። ልጅዎ ከኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውጪ ክትባት ከወሰደ፣ DOCIIS ውስጥ ላይገኝ ይችላል።

### 5። የልጄን የክትባት ማስረጃ ለልጄ ትምህርት ቤት እንዴት ማቅረብ እችላለሁ?

DOCIIS ልጅዎ ሁሉንም አስፈላጊ የሆኑ ክትባቶች እንደወሰደ የማያሳይ ከሆነ፣ ትምህርት ቤቱ ማስረጃ የሚጠይቅ ይሆናል። የተሟላ አለም አቀፍ የጤና ምስክር ወረቀት (የሚመከር) ወይም ሌላ ከሃኪምዎ የተሰጠ የሃኪም ማህተም፣ ማህተም ወይም ፊርማ ያለበት ይፋዊ መዝገብ የመሳሰሉ የጽሁፍ መዝገቦችን ሊሰጧቸው ይችላሉ።[3] ከዚያም ትምህርት ቤቱ ይህንን መረጃ በ DOCIIS ወይም በልጅዎ የጤና ፋይል ውስጥ ያስቀምጠዋል። ከዲሴምበር 31 በፊት የተያዘ የክትባት ቀጠሮ ካርድ ካለዎት፣ ለጊዜው መስፈቶቹን ለማሟላት ካርዱን መጠቀም ይችላሉ፣ ነገር ግን በጊዜያዊነት ከትምህርት ቤት ከመቅረት ለመቆጠብ የክትባቱን ማረጋገጫ በቀጣዩ የትምህርት ቀን ማሳየት አለብዎት (ከመገለል ቀን፣ ዲሴምበር 9 በኋላ ከሆነ)።

### 6። ልጄ ሁሉም ክትባቶቹን/ቿን ካልወሰደ/ች፣ ትምህርት ቤት መሄድ ይችላል/ትችላለች?

ክትባቶች ተማሪዎችን እና የትምህርት ቤት ማህበረሰቦችን ጨምሮ ሁሉንም ሰው ለመጠበቅ አስፈላጊ ናቸው። ተማሪዎች በተወሰኑ እድሜዎች፦ ከ pre-K 3፣ መዋለህጻናት፣ 7ኛ ወይም 11ኛ ክፍል ላይ ተጨማሪ ክትባቶችን እንዲያገኙ ይገደዳሉ። በእነዚህ ክፍሎች ያሉ ተማሪዎች ያለ ክትባት ማስረጃ ትምህርት ቤት መሄድ የሚችሉት ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው። ልጅዎ pre-K 3፣ መዋለህጻናት፣ 7ኛ ወይም 11ኛ ክፍል ከሆነ/ች እና ሁሉም አስፈላጊ የሆኑት ክትባቶች ከሌለው/ላት ትምህርት ቤቱ የክትባቶችን ማስረጃ ለማሳየት ቀን የሚኖርዎት እስከ ዲሴምበር 9 መሆኑን የሚገልጽ ደብዳቤ የሚልክልዎ ይሆናል። መረጃውን ካላቀረቡ፣ ልጅዎ ክትባቶቹን እስኪወስድ እና ማስረጃውን ለትምህርት ቤቱ እስከሚሰጡ ድረስ ወደ ትምህርት ቤት እንዲመለስ አይፈቀድለትም።

### 7። ልጄ ሁሉንም አስፈላጊውን ክትባቶች ካልወሰደ/ች ምን ይፈጠራል?

ልጅዎ ሁሉንም አስፈላጊ የሆኑ ክትባቶቻቸውን ካልወሰዱ፣ ትምህርት ቤቱ የትኞቹ ክትባቶች እንዳመለጡት የሚገልጽ ደብዳቤ የሚልክልዎ ይሆናል። እንዲሁም በ pre-K 3፣ መዋለህጻናት፣ 7ኛ ወይም 11ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች እስከ ዲሴምበር 9 ድረስ የክትባቶች ማስረጃ ካላሳዩ ትምህርት ቤቱ ልጅዎ በጊዜያዊነት እንደሚባረር የሚገልጽ ማስጠንቀቂያ የሚልክልዎ ይሆናል።

OSSE
DC HEALTH
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
WE ARE WASHINGTON DC
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

ወዲያውኑ ከልጅዎ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ጋር ቀጠሮ ሊይዙ ይገባል። እስከ ዲሴምበር 9 ድረስ የክትባቶች ማስረጃ ካላሳዩ፣ ልጅዎ ክትባቶቹን እስኪወስድ እና ማስረጃውን ለትምህርት ቤቱ እስከሚሰጡ ድረስ ወደ ትምህርት ቤት እንዲመለስ አይፈቀድለትም።

የክትባቶች ማስረጃ እስከሚያሳዩ ድረስ ለሚያመልጠው እያንዳንዱ የትምህርት ቀን ልጅዎ "ይቅርታ የማይደረግበት ቀሪ" ይኖረዋል። አንድ ጊዜ ትምህርት ቤት ማስረጃውን ካገኘ፣ ልጅዎ ወደ ትምህርት ቤት መመለስ ይችላል እና እያንዳንዱ ያለፉት ቀናት "ይቅርታ ወደሚደረግበት ቀሪ" የሚቀየር ይሆናል።

### 8። ልጄ ሁሉንም የሚፈለጉ ክትባቶችን እንደወሰደ ካመንኩ ፣ነገር ግን ትምህርት ቤቱ ልጄ አንድ ወይም ከዚያ በላይ እንዳመለጠው ቢነግረኝ ምን ማድረግ እችላለሁ?

a። የልጅዎ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ጋር ያጣሩ፦ ልጅዎ አስፈላጊ የሆኑ ክትባቶችን ተከትቦ እንደሆነ ይጠይቁ።

- ከተከተቡ፣ የሃኪም ማህተም፣ ማህተም ወይም ፊርማ ያለበት የጽሁፍ ማስረጃ ይጠይቁ።
- ካልተከተቡ፣ ለክትባቶች ወዲያውኑ ቀጠሮ ይያዙ።

b። የጽሁፍ ማስረጃ ያግኙ፦ ቀጠሮው ላይ፣ ሃኪሙ አለም አቀፍ የምስክር ወረቀቱን (የሚመከር) ወይም ሌላ የሃኪም ማህተም፣ ማህተም ወይም ፊርማ ያለበት ቅጽ እንዲሞላ ያድርጉ።[3]

c። ማስረጃውን ለትምህርት ቤቱ ይስጡ፦ ትምህርት ቤቱ ወደ ልጅዎ የጤና ፋይል እንዲያክላቸው ሰነዶቹን ለልጅዎ ትምህርት ቤት ይስጡ።

### 9። ልጄ መከተብ የማይችል ቢሆን ምን ይሆናል?

ልጅዎ በህክምና ምክንያቶች ክትባቶችን መውሰድ ካልቻለ፣ በህክምና ነጻ መደረግ ማግኘት ይችላሉ። ይህንን ነጻ መደረግ የግል ሃኪም ወይም የህዝብ ጤና ባለስልጣን መፈረም አለበት። ለሃይማኖታዊ ነጻ መደረጎች፣ የ DC Health ድረገጽን ይመልከቱ። ለትምህርት ቤቱ የ DC Health አመታዊ ሁማን ፓፒሎማቫይረስ (HPV)ክትባት መርጦ የመውጣት ምስክር ወረቀት በመስጠት ከ HPV ክትባት መርጠው መውጣት ይችላሉ።[8]

### 10። ለልጄ ላገኝ የምችለው የቀደመ ቀጠሮ የትምህርት ዓመቱ ከጀመረ በኋላ ከሆነስ?

የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች በትምህርት መጀመሪያ ላይ ስራ ሊበዛባቸው ይችላል ስለዚህ ቀደም ብለው ያቅዱ። ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ልጅዎ ሁሉም አስፈላጊ የሆኑ ክትባቶችን እንዳገኘ ያረጋግጡ። በ DC Health ድረገጽ ላይ የህጻናት ህክምና የክትባት ቦታዎችን ዝርዝር ማግኘት ይችላሉ።[3]

### 11። እኔ ቀዳሚ የእንክብካቤ አቅራቢ ወይም የህክምና መድን ከሌለኝ ምን ይሆናል?

እርስዎ ወይም ልጅዎ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ከሌለዎት፣ የመድን ዋስትና ኩባንያዎ በአቅራቢያዎ የሚገኝ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ እንዲያገኙልዎ ይደውሉ። የመድን ዋስትና ከሌለዎት፣ DC Health Link ወይም ወደ 3-1-1 በመደወል ከተማ አቀፍ የጥሪ ማዕከልን (Citywide Call Center) ያነጋግሩ።[9]

### 12። ሌላ አገር የተገኘ የክትባቶች ሰነድ ካለኝ ምን ይሆናል?

ልጅዎ ሌላ አገር ከተከተበ፣ ስለ ሰነዱ የትምህርት ቤትዎን ነርስ ወይም የትምህርት ቤቱ የክትባት ተጠሪ (IPOC)ን ይጠይቁ። ሰነዱ መስፈርቶቹን ያሟላ እንደሆነ ወይም ተጨማሪ እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልግዎ እንደሆነ ለማየት ከ DC Health ጋር የሚያጣሩ ይሆናል።

### 13። እኔ ትምህርት ቤት በአካል ለመማር ወይም ለሌሎች እንቅስቃሴዎች ስለሚያስፈልጉ ክትባቶች ወይም የክትባት መስፈርቶች ጥያቄዎች ካለኝስ ምን አደርጋለሁ?

ስለ ክትባቶች እና መርጃዎች ጥያቄዎች ካለዎት፣ የ DC Health የክትባት ፕሮግራምን በ(202) 576-7130 ያነጋግሩ ወይም ድረገጻቸውን በ dchealth.dc.gov/immunization ይጎብኙ። ስለ ትምህርት ቤት የክትባት ፖሊሲ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ ትምህርት ቤትዎን ወይም የአካባቢ የትምህርት ድርጅት (LEA) ማዕከላዊ ቢሮን ያነጋግሩ። እንዲሁም ለOSSE በOSSE.SchoolHealth@dc.gov ኢሜይል መላክ ይችላሉ።[10]

ይህ አዘውትረው የሚጠየቁ ጥያቄዎች እና መልሶች ከጊዜ በኋላ ይሻሻላል።
በመጨረሻ የተሻሻለበት ቀን፣ ጁላይ 31፣ 2024

**የግርጌ ማስታወሻዎች**

1 DC Official Code § 38–501 et seq፣ code.dccouncil.us/dc/council/code/titles/38/chapters/5/

2 DCMR 5-E § 5300 et seq.፣ dcregs.dc.gov/common/dcmr/rulelist.aspx?ChapterNum=5-e53&chapterid=258

3 dchealth.dc.gov/immunization

4 cdc.gov/vaccines/parents/FAQs.html

5 cdc.gov/vaccines/parents/why-vaccinate/vaccine-decision.html

6 cdc.gov/vaccines/parents/diseases/hpv.html

7 DCMR 22-B §§ 130-152: dcregs.dc.gov/Common/DCMR/RuleList.aspx?ChapterNum=22-B1&ChapterId=576

8 dchealth.dc.gov/service/immunization-forms

9 dchealthlink.com

10 osse.dc.gov/immunization